# 6ኛ ዓመት የቀይ ሽብር ሰማዕታት ቀን
# በአሲምባ የውይይት መድረክ

ቅዳሜ ጳጉሜ 3 ቀን 2004 ዓ.ም.
September 8, 2012

መጪው ቅዳሜ ጳጉሜ 3 ቀን (September 8, 2012) 6ኛው ዓመት የቀይ ሽብር ሰማዕታት ቀን በአሲምባ የውይይት መድረክ በተለያዩ ዝግጅቶች ተከብሮ ይውላል። በዚህ ዓመት የተለያዩ እንግዶች ከመካከላችን በመገኘት የዚያን ትልድ ሰማዕትነትና ለወገኑ የከፈለውን ገድል አብረን የምናከብርበት፣ ከሁሉም በላይ የተዋደቁለት የኢትዮጵያ ሕዝብ መብት ዛሬም ትግሉ የቀጠለ በመሆኑ ሁላችንም በአንድነት ትግላቸውን ለማስቀጠል ቃል የምንገባበት ነው።

በክብር እንግድነትም በቅርቡ በሰሜን አሜሪካ ዳንቨር ኮሎራዶ የአሜሪካን ደህንነት ኃይሎች ቁጥጥር ሥር የዋለው የከፍተኛ 15 የቀይ ሽብር ተዋንያን ቁንጮ የነበረው የከፍያለው ዓለሙ ቀትተኛ ተጠቂ የነበረ ወገን ከመካከላችን ይገኛል።

የአሲምባ ውይይት መድረክ የተመሠረተበት ዋና ምክንያት በደርግ ፋሺሽታዊ ሥርዓትና በጎሣ ፖለቲከኞች ካለፍርድ የተጨፈጨፉትን የዚያን ትውልድ ወገኖች የምናስታውስበት፤ የትግል ታሪካቸውን የምንነግርበትና ሌላ ቀይ ሽብር በሀገራችን በማንም ገዢ እንዳይደገም ሕብረተሰባችን ግንዛቤን እንዲያገኝ የምንቀሰቅስበት መድረክ እንዲሆን ታስቦ ስለሆነ በየዓመቱ እነሆ ዘንድሮ ለ6ኛ ጊዜ ይህንን ዝግጅት ይዘን ቀርበናል።

አሲምባ በየሳምንቱ ቅዳሜ የጊዜውን የሀገራችንን ፖለቲካዊ ሁናቴ በመርመር በሳል ሃሳቦች የሚንሸራሸሩበት ዴሚክራሲያዊ ነጻ የውይይት መድረክ ነው። ዝግጅታችን እንደ ዋሺንግተን ዲሲ ሰዓት አቆጣጠር ከቀኑ 2 ሰዓት ይጀመራል።

የአሲምባ ውይይት መድረክ